EFDA
የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን
ETHIOPIAN FOOD & DRUG AUTHORITY

ከኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን
ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# የመድኃኒት አግባባዊ አጠቃቀም ለስኬታማ ሕክምና ያለው ፋይዳ

የመድኃኒት አግባባዊ አጠቃቀም ማለት የተለያዩ የጤና ችግሮችን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር ወይም ለመግታት የሚያስችል መድኃኒትን በትክክለኛ መንገድ መጠቀም ነው። በሌላ አገላለፅ በምርመራ ለተረጋገጠ በሽታ ትክክለኛው መድኃኒት ለታማሚው በጊዜና በመጠን ሲሰጥና ታማሚውም መድኃኒቱን በትክክል ሲወስድ አግባባዊ የመድኃኒት አጠቃቀም ይባላል።

ይሁንና በትክክል ተመርምሮ የትኛው ዓይነት በሽታ አምጪ ተህዋስ እንዳስከተለው ለማይታወቅ በሽታ፣ በሐኪም ከታዘዘው መጠን በታች (በላይ) ሲወሰድ፣ መወሰድ ከነበረበት ሠዓት ታልፎ ወይም ቀድሞ ሲወሰድ፣ የታዘዘውን ጸረ-ተህዋስ መድኃኒት ሙሉ በሙሉ ሳይወስዱ ከቀረ (ከተቋረጠ) እና የመሳሰሉት ድርጊቶች ሲፈፀሙ ያኔ ትክክለኛ ያልሆነ የመድኃኒት አጠቃቀም ተከሰተ ልንል እንችላለን።

አግባባዊ የመድሃኒት አጠቃቀም ጤናን ለመጠበቅ እና የተለያዩ የጤና ችግሮችን ለመቀነስ እጅግ አስፈላጊ ሲሆን በሽታውን ከመለየት ወይም በትክክለኛው መንገድ በሽታውን መርምሮ ከማወቅ ይጀምራል። በመቀጠልም ላወቁት በሽታ ትክክለኛ መድኃኒት መጠኑን /ዶዙን/ የሚወሠድበትን የጊዜ መጠን፣ የመድኃኒቱ ከበሽታው ከሌሎች መድኃኒቶች ከምግብና ከሠዎች ጋር ያለውን መስተጋብር ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ እና የመግዛት አቅሙን ባማከለ ሁኔታ መድኃኒቱን መምረጥና ከትክክለኛ የመድኃኒት አጠቃቀም ጋር ይታዘዛል።

በመቀጠልም የመድኃኒት አዳዩ /የፋርማሲ ባለሙያው/ ሐኪሙ ያዘዘውን ትክክለኛ መድኃኒት በትክክለኛ ጥራት ፤ ተገቢ የመድኃኒት መረጃና ከአግባባዊ የመድኃኒት አጠቃቀም ምክር ጋር ሲያድል ነው። መድኃኒቱ የታዘዘለት ግለሠብም በታዘዘለት የመድኃኒት አወሳሰድ መሠረት እንደታዘዘለት የአወሳሰድ ምክር መውሠድ ሲችል አግባባዊ የመድኃኒት አጠቃቀም ሠፈነ እንላለን።

ሌላው መሠረታዊ ነገር ተደርጎ የሚወሰደው መድኃኒት ሀኪሙ ባዘዘው ትክክለኛ መጠን ሊሆን ይገባል። ይህ ሲባል መድኃኒቱን የሚወስደው ሰው የመድኃኒቱን መጠን መጨመር ወይም መቀነስ አይገባውም ማለት ነው። ምክንያቱም የመድኃኒቱን መጠን መቀነስ ከህመማችን ለመፈወስ ስለማያስችለን ሲሆን የመድኃኒት መጠኑን መጨመር ደግሞ ለሌላ የጤና ጉዳት ሊዳርገን ስለሚችል ነው። ስለሆነም ከሕክምናችን ተፈላጊውና ተጠባቂውን ውጤት ለማግኘት መድኃኒት ያለምንም ማቋረጥ በአግባቡ ሊወሰድ ያስፈልጋል።

ከዚህ በተጨማሪ በአግባባዊ የመድኃኒት አጠቃቀም ላይ ሊነሳ የሚገባው ጉዳይ የመድኃኒቱ አይነት ሲሆን በዚህም በሀኪሙ የታዘዘው መድኃኒት ብቻ መወሰድ አለበት። ይህ ሲባል የተለያዩ መድኃኒቶችን በማዋሃድ መውሰድ ከፍ ላለ ጉዳት ሊዳርግ እንደሚገባ ልብ ሊባል ይገባዋል። በተለይ የመድኃኒት አዎንታዊ እና አሉታዊ ተጽዕኖዎች ማወቅ ለአግባባዊ የመድኃኒት አጠቃቀም ወሳኝ ጉዳይ ሲሆን የመድኃኒት አደገኛ ውጤቶችን ለመከላከል ሚናው ላቅ ያለ ነው። ምክንያቱም መድኃኒቶቹ የሚያደርሱትን አሉታዊ ውጤቶች ተገንዝቦ መድኃኒቱን ሳያቋርጡ ለመውሰድ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል።

ሌላው መድኃኒት በትክክለኛ መንገድ ማስቀመጥ ወሳኝ የአግባባዊ የመድኃኒት አጠቃቀም ጉዳይ ሲሆን መድኃኒት በቀዝቃዛ፣ ደረቅ እና ጨለማ ቦታ መቀመጥ ይኖርባቸዋል። ከህፃናት እና ከቤት እንስሳት ተጠብቆ ማስቀመጥም እንዲሁ። እርስ በእርሳቸው ተቃርኖ የሚፈጥሩ መድኃኒቶችን መጠቀም አይገባም። በተጨማሪም ትክክለኛ የመድኃኒት አጠቃቀም የጤና ችግሮችን በተገቢው መንገድ ለመቆጣጠር ይረዳል።

እንዲሁም ለራስ የታዘዘን መድኃኒት ለሌሎች ማጋራት በፍፁም የማይመከር ተግባር ሲሆን ይህ ደግሞ የመድኃኒት አደገኛ ውጤቶችን ለመከላከል እና የጤና አጠቃላይ ሁኔታን ለማሻሻል ትልቅ አስተጽኦ አለው ። ስለዚህ የመድኃኒት አጠቃቀምን በትክክል ለመከተል የህክምና ምክር መከተል ያስፈልጋል።

የመድኃኒት አጠቃቀም የጤና ችግሮችን ለመቆጣጠር እና ለመከላከል ዋነኛው መንገድ ነው። ሆኖም ትክክለኛ መንገድ ሳይከተል መድኃኒትን መጠቀም አደገኛ ውጤቶችን ሊያስከትል ይችላል። ስለሆነም የመድኃኒት አግባባዊ አጠቃቀም ሕግጋትን እና የህክምና ምክሮችን በመከተል የጤና ችግሮችን በተገቢው መንገድ ለመቆጣጠር ይረዳል። ይህ ደግሞ የመድኃኒት አደገኛ ውጤቶችን ለመከላከል እና የጤና አጠቃላይ ሁኔታን ለማሻሻል ያስችላል።

በመሆኑም የመድኃኒት አደገኛ ውጤቶችን ለመከላከል ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል። የመድኃኒት ዓላማ ህመምን ማስወገድ ብቻ ሳይሆን የጤና አጠባበቅን ማረጋገጥ ነው። የመድኃኒት ለውጦችን ካስተዋሉ ወዲያውኑ ዶክተርን ማሳወቅ አለበት።

መድኃኒትን በአግባቡ አለመጠቀም ደግሞ የተለያዩ ጉዳቶች ሲኖሩት ከእነዚህ ችግሮች አንዱ የጸረ-ተህዋሲያን መድኃኒቶች መላመድ ነው። የጸረ-ተህዋሲያን መድኃኒቶች መላመድ ማለት ከዚህ ቀደም በበሽታ አምጪ ተህዋሲያን አማካኝነት የሚመጡ በሽታዎችን ለማከም ሆነ ለመከላከል ሲሰጥ የነበረው አንድ ጸረ-ተህዋስ መድኃኒት ሲሰጥ በነበረው መጠን ወይም ከዚያም በላይ የሰውነትዎ ሴሎች ሊቋቋሙት በሚችሉት መጠን ሁሉ ሲሰጥ ተህዋሲያኑ የማይሞቱ ወይም መራባትን የማያቆሙ እና ህመምተኛው ከህመሙ የማይፈወስ ከሆነ ተህዋሱ ከመድኃኒት ጋር ተላምዷል ይባላል። በዚህ የተነሳ መድኃኒቱን በተላመደ ተህዋስ የታመመ ታካሚ ምንም እንኳን በሽታው በትክክል ታውቆ መድኃኒቱን እየወሰደ ቢሆንም ከበሽታው የማይፈወስ ይሆናል።

እዚህ ጋር መታየት ያለበት ነገር የአንድን መድኃኒት የሚወሰደውን መጠን እየጨመርን ስንሄድ ምላሹ በዚያው መጠን ከፍ የሚል ወይም ያንን መድኃኒት ካልወሰድን ከህመማችን የምንፈወስበት ጊዜ ይኖራል። ይህ ሒደት መላመድ፣ ብግርነት ወይም መቋቋም ይባላል።

ለምሳሌ የዚህ ዓይነት ባህሪ ከሚያሳዩ መድኃኒቶች መካከል የህመም ማስታገሻ መድኃኒቶች፣ የቲቢ እንዲሁም የናርኮቲክ እና የሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ተጠቃሽ ናቸው።

የመድኃኒቶች ከጀርሞች ጋር መላመድ ሲባል ግን የሰውነት ሴሎች በሚቋቋሙት መጠን ሁሉ ሲሰጥ ከሕመም የማይፈወስ ሲሆኑ ነው። ይህም ማለት መጠንን መጨመር ወይም መድኃኒቱን መውሰድ ትርጉም አይኖረውም ማለት ነው፤ መድኃኒቱ ከጥቅም ውጭ ሆኗልና።

ሁሉም የጸረ-ተህዋሲያን መድኃኒቶች ማለትም ጸረ-ባክቴሪያ (አንቲባዮቲክ) መድኃኒቶች፣ ጸረ-ቫይረስ መድኃኒቶች፣ ጸረ ፈንገስ መድኃኒቶች እና ጸረ-ፕሮቶዝዋ በበሽታ አምጪ ጀርሞች ይላመዳሉ።

ምንም እንኳን አብዛኛዎቹ መድኃኒቶች በሀኪም ትዕዛዝ ብቻ የሚወሰዱ ቢሆኑም ጥቂት መድኃኒቶች ግን የሀኪም ማዘዣ ወረቀት ሳያስፈልግ ሰዎች በቀላሉ ከመድኃኒት ቤቶች ገዝተው ሊጠቀሙባቸው የሚችሉም አሉ። አግባባዊ የመድሃኒት አጠቃቀም አላስፈላጊ የሆኑ ግብረ ምልከታዎችን እና ተጨማሪ ሕክምናዎችን ለማስወገድ ይረዳል። ይህም የጤና እንክን ወጪዎችን ይቀንሳል። በመሆኑም ማንኛውም መድኃኒት ከመውሰዳችን በፊት ከጤና ባለሙያ ምክር መወሰድ የግድ ይለናል ምክንያቱም ማንኛውም መድኃኒት ያለ መድኃኒት መረጃ መጠቀም ኬሚካል ወይም መርዝ እንደመውሰድ ተደርጎ ስለሚቆጠር ነው።

Tel : +251-11-552-41-22
+251-11-552-41-22
P.o.box. 5681
Free call. 8482

http://www.fmhaca.gov.et/contact/
E-mail contactefda@efda.gov.et
Telegram channel link
https://t.me/ethiopianfoodanddrugauthority/